Intriem Task Force of Andenet Support Chapters in Europe
በአውሮፓ የአንድነት ድጋፍ ድርጅቶች አስተባባሪ ግብረ ኃይል

# የነጻነት ዓርበኞች እንጂ ለነጻነት የሚደረገውን ትግል መግደል አይቻልም፣

ሀገራችን ኢትዮጵያን ለማስተዳደር የህግም ሆነ የሞራል ሥልጣን የሌለው፣ የመለስ ዜናዊ የሚመራው የወያኔ /ኢህአዴግ ገዥ ሥርዓት፣ በወገናችን ላይ የሚፈጽመው ግፍ ማጠራቀሚያ ጽዋው ሞልቶ ከፈሰሰ ውሎ አድሯል። ህዝብ በሰዕባዊነት እና በዜግነት የተጎናጸፈውን መብት ተገፎ፣ በጠመንጃ እየተረገጠ የሚገዛበት አስከፊ የግፍ ቀንበር ተጭኖበት ሀገራችን ዛሬ ነጻነታቸውን የሚጠይቁ ዜጎች የሚገደሉበት እና የሚታጎሩበት እሥር ቤት ሆናለች።

ኢተዮጵያ ዛሬ የኢኮኖሚ ፣ የማህበራዊ ፣ የመገናኛ ፣ የደህንነት እና የመከላከያ አውታሮች በገዥው ቡድን ቁጥጥር ሥር ሆነው፣ ሰርቶ የማግኘት ፣ ሀገርን የማገልገል፣ የትምህርት እድልን በነጻ የመዘዋወር መብቶች ለጥዊቶች የተፈቀደ ብዙሀኑ አንገቱን ደፍቶና ተሸማቆ በሁለተኛ ዜጋነት የሚኖርባት የአፓርታይድ ሥርዓት የነገሰባት ሀገር ሆናለች።
በመጭው የ2002 ዓም የይስሙላ ምርጫ፣ የምርጫ ቦርድ፣ የመገናናኛ ብዙሀን፣ የፍትህ ሥርዓቱ፣ በገዥው ፓርቲ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ሆነው፣ ተቃዋሚዎች ህዝቡን የማግኘት እና የሚያስተዳድረውን መንግስት በነጻ የመምረጥ መብቱ እንዲከበር ለማስተማር መንቀሳቀስ አዳጋች በሆነበት እና የህዝብ ድምጽ መቁጠር ዋስትና በሌለበት ሁኔታ፣ ፍትሀዊ ምርጫ ይደረጋል ብሎ ህዝብን እና የዓለም አቀፍ ማህበረሰብን ለማሞኘት የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት ሽር ጉድ ላይ ይገኛል።

ለነጻነት እና ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ሀይሎች ይህንን አስከፊ ሥርዓት ለመታገልና ብሎም በብሄራዊና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመተካት በመድረክ ዙሪያ ተሰባስበው፣ የህዝብ መሰረት የሌለውን የአምባገነን አገዛዝ በመታገል ላይ ይገኛሉ። በእሥር ቤት የምትገላታው ለነጻነት፣ ለፍትህንና ለዴሞክራሲ ለሚደረገው ትግል ፈርጥ የሆነችው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የምትመራው ፓርቲና የመድረኩ አባላት፣ በገዥው ፓርቲ ቀጥተኛ ትእዛዝ የሚደረግባቸው እንግልት እና ወከባ ሳይበግራቸው ለነጻነት እና ለዴሞክራሲ መስፈን የህይወትም መስዕዋትነት ጭምር እየከፈሉ ይገኛሉ።

መድረክን ወክለው በዓድዋ አካባቢ ለህዝብ ተወካይነት ሊወዳደሩ የነበሩት የነጻነት ዓርበኛ፣ አቶ አረጋዊ ገብረዮሀንስ በአመኔያዊ ሁኔታ በወያኔ ታጣቂዎች ተገለዋል። በተጨማሪም በአክሱም የውቅሮ ወረዳ ተወዳዳሪ፣ አቶ አያሌው አየለ በወያኔ ታጣቂዎች በደረሰባቸው ከፍተኛ ድብደባ፣ ህይወታቸው በሞት አፋፍ ላይ ይገኛል።

ለአንድነት፣ ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ዜጎች ላይ የሚፈጸመው ግፍ፣ የሥርዓቱን አምባገነናዊ ገጽታ መባባስ ሲያመለክት፣ በአንጻሩ የበልጡኑ እየተጠናከረ የመጣው የነጻነት ፍላጎት እና ለመስዕዋትነት ያለው ዝግጁነት፣ የዓምባገነኑ ሥርዓት ህዝብ ለነጻነት እና ለዴሞክራሲ መሰፈን ያለውን ፍላጎት ሊያስረው ወይም ሊገድለው እንደማይችል ይመሰክራል።

እኛም በአውሮፓ የምንገኝ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች፣ በአቶ አረጋዊ ገብረዮሀንስ ሞት የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እየገለጽን፣ ለቤተሰባቸው እና

ለዘመዶቻቸው እግዚህብሄር ጽናት እና ጥንካሬ ይሰጣቸው እያልን፣ በዚህ የአፈና ሥርዓት ውስጥ ለምትንገላቱ የነጻነት እና የዴሞክራሲ አርበኞች በሙሉ፣ በዚህ እልህ አስጨራሽ

ትግል ከጎናችሁ የምንቆም ለመሆናችንና ለሀገራችን ትንሣኤ በምታደርጉት ተጋድሎ ሁሉ በደጀንነት መሰለፋችንን እናረጋግጣለን።

በሀገርም፣ ከሀገር ውጭ ለምትገኙ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ፣ በሀገራችን ላይ ያንዣበበው የአፈና ደመና እንዲገለጥ በሚደረገው ትግል የተቻላችሁን ትብብር እና ዓስተዋጽዖ እንድታደርጉ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ተጋድሎ ነጻ ትወጣለች !!!**
**የአውሮፓ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች አስተባባሪ ግብረ ሀይል፣**

**መጋቢት 2002 ዓም**